# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት – አንደኛ

## የሕይወት ቃል

1 ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውን፣ የሰማነውን፣ በዐይኖቻችን ያየነውን፣ የተመለከትነውንና እጆቻችን የዳሰሱትን እንናገራለን። 2ሕይወት ተገለጠ፤ እኛም አይተነዋል፤ እንመሰክርለታለንም። በአብ ዘንድ የነበረውን፣ ለእኛም የተገለጠልንን የዘላለም ሕይወት እንነግራችኋለን፤ 3እናንተም ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ፣ ያየነውንና የሰማነውን እንነግራችኋለን፤ ኅብረታችንም ከአብ፣ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው። 4ደስታችንም[ሀ] ፍጹም ይሆን ዘንድ ይህን እንጽፍላችኋለን።

## በብርሃን መመላለስ

5 ከእርሱ የሰማነው ለእናንተም የምንነግራችሁ መልእክት፣ እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም፤ የሚል ነው። 6በጨለማ እየተመላለስን ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል እንዋሻለን፤ እውነትንም አንኖረውም። 7ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ፣ እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ በእርሳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ[ለ] ያነጻናል።

8ኀጢአት የለብንም ብንል፣ ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። 9ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው። 10ኀጢአት አልሠራንም ብንል፣ እርሱን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፤ ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።

2 ልጆቼ ሆይ፤ ይህን የምጽፍላችሁ ኀጢአት እንዳትሠሩ ነው፤ ነገር ግን ማንም ኀጢአት ቢሠራ፣ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። 2እርሱም የኀጢአታችን ማስተስረያ ነው፤ ይኸውም[ሐ] ለዓለም ሁሉ ኀጢአት እንጂ ለእኛ ብቻ አይደለም።

3ትእዛዛቱን ብንፈጽም እርሱን ማወቃችንን በዚህ ርግጠኞች እንሆናለን። 4 "እርሱን ዐውቃለሁ" እያለ ትእዛዙን የማይፈጽም ግን ሐሰተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም። 5ነገር ግን ማንም ቃሉን ቢጠብቅ፣ በእውነት የእግዚአብሔር ፍቅር[መ] በእርሱ ፍጹም ሆኖአል። በእርሱ መሆናችንን የምናውቀው በዚህ ነው፤ 6ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል።

7ወዳጆች ሆይ፤ የምጽፍላችሁ፣ ከመጀመሪያ የነበራችሁን የቈየውን ትእዛዝ እንጂ አዲስ ትእዛዝ አይደለም፤ የቈየው ትእዛዝ የሰማችሁት ቃል ነው። 8 በሌላ በኩል የምጽፍላችሁ ጨለማው ዕያለፈና እውነተኛው ብርሃን እየበራ ስለሆነ፣ በእርሱም፣ በእናንተም ዘንድ እውነት የሆነውን አዲስ ትእዛዝ ነው። 9በብርሃን አለሁ የሚል፣ ወንድሙን ግን የሚጠላ አሁንም በጨለማ ውስጥ አለ። 10ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል፤ በእርሱም ዘንድ የመሰናከያ ምክንያት የለውም። 11ነገር ግን ወንድሙን የሚጠላ በጨለማ ውስጥ ነው፤ በጨለማ ይመላለሳል፤ ጨለማው ስላሳወረውም የት እንደሚሄድ አያውቅም።

12ልጆች ሆይ፤
ኀጢአታችሁ ስለ ስሙ ተሰርዮላችኋልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
13አባቶች ሆይ፤
ከመጀመሪያ ያለውን እርሱን
ዐውቃችሁታልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
ጐበዛዝት ሆይ፤ ክፉውን
አሸንፋችኋልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
ልጆች ሆይ፤
አብን ዐውቃችሁታልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
14አባቶች ሆይ፤
ከመጀመሪያ ያለውን እርሱን
ዐውቃችሁታልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
ጐበዛዝት ሆይ፤
ብርቱዎች ስለሆናችሁ፣
የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ስለሚኖር፣
ክፉውንም ስላሸነፋችሁ፣
እጽፍላችኋለሁ።

## ዓለምን አትውደዱ

15ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማናቸውንም ነገር አትውደዱ፤ ማንም ዓለምን ቢወድ፣ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤

1፥1 ሉቃ24፥48፤ ዮሐ 1፥2፡14፤19፥35፤20፥27፤ ሐሥ4፥20፤2ጴጥ1፥16፤ 1ዮሐ4፥14
1፥2 ማቴ25፥46፤ ዮሐ1፥1-4፤11፥25፤ 14፥6፤15፥27፤ቲቶ 3፥16፤1ጴጥ1፥20፤ 1ዮሐ3፥5፡814፤11፥25 ፤14፥6፤15፥27፤ቲቶ 3፥16፤1ጴጥ1፥1፥20፤ 1ዮሐ3፥5፡8
1፥3 ቍ1፤1ቆሮ1፥9
1፥4 ዮሐ3፥29፤ 1ዮሐ2፥11
1፥5 1ጢሞ6፥16፤ 1ዮሐ3፥11
1፥6 ዮሐ3፥19-21፤ 8፥12፤2ቆሮ6፥14፤ ኤፌ5፥8፤1ዮሐ2፥4፡ 11፤4፥20
1፥7 ኢሳ2፥5፤ዕብ9፥14 ፤ራእ1፥5፤7፥14
1፥8 ምሳ20፥9፤ ኤር2፥35፤ዮሐ8፥44፤ ሮሜ3፥9-19፤ያዕ3፥2 ፤1ዮሐ2፥4
1፥9 ቍ7፤መዝ 32፥5፤51፥2፤ምሳ 28፥13፤ሚክ7፥18-20 ፤ዕብ10፥22
1፥10 ቍ8፤ዮሐ5፥38 ዮሐ5፥38፤1ዮሐ2፥14 ፤5፥10
2፥1 ቍ12፡13፡28፤ ሮሜ8፥34፤1ተሰ2፥11፤ 1ጢሞ2፥5፤1ዮሐ3፥7፡ 18፤4፥4፤5፥21
2፥2 ማቴ1፥21፤ዮሐ 3፥17፤ሮሜ3፥25፤1ዮሐ 4፥10፤ሚኪ7፥18-20
2፥3 ቍ4፡5፤ዮሐ 14፥15፤1ዮሐ3፥24፤ 4፥13፤5፥2
2፥4 ቍ3፤ቲቶ1፥16 ፤1ዮሐ1፥6፡8፤3፥6፤ 4፥7፡8
2፥5 ቍ3፤ዮሐ14፥15 ፤1ዮሐ4፥12
2፥6 ማቴ11፥29
2፥7 ቍ24፤1ቆሮ 10፥14፤1ዮሐ3፥11፡ 23፤4፥21፤2ዮሐ5፡6
2፥8 ዮሐ19፤13፥34፤ ሮሜ13፥12፤ኤፌ58፤ 1ተሰ5፥5፤ዕብ10፥25
2፥9 ቍ11፤ዘሌ 19፥17፤1ዮሐ1፥5፤ 3፥10፡15፡16፤4፥20፡21
2፥10 ቍ11፤መዝ 119፥165፤1ዮሐ3፥14
2፥11 ቍ9፤ዮሐ 11፥9፤12፥35፤1ዮሐ1፥6
2፥12 ቍ1፤1ዮሐ3፥23
2፥13 ቍ1፡14፤ማቴ 5፥37፤ዮሐ1፥1፤16፥33
2፥14 ቍ13፤ዮሐ 1፥1፤5፥38፤ኤፌ6፥10፤ዕብ4፥12፤1ዮሐ1፥10
2፥15 ሮሜ12፥2፤ያዕ4፥4

[ሀ]4 አንዳንዶች ቅጆች *የእናንተ* ይላል
[ለ]7 ወይም *ከማንኛውም*
[ሐ]2 *ኀጢአታችንን አስወግዶ የእግዚአብሔርን ቍጣ ከእኛ የሚያርቅ እርሱ ነው ይኸውም የእኛን ኀጢአት ብቻ ሳይሆን ማለትም ነው።*

16ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ:- የሥጋ
ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት
ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም::
17ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን
ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል::

### ከክርስቶስ ተቃዋሚዎች መጠንቀቅ

18ልጆች ሆይ፤ ይህ የመጨረሻው ሰዓት
ነው፤ እንደሰማችሁትም የክርስቶስ ተቃዋሚ
ይመጣል፤ አሁን እንኳ ብዙ የክርስቶስ ተቃ
ዋሚዎች መጥተዋል፤ የመጨረሻው ሰዓት
እንደ ሆነ የምናውቀውም በዚህ ነው::
19ከእኛ መካከል ወጡ፤ ይሁን እንጂ
ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገን ቢሆ
ኑማ ኖሮ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር::
ነገር ግን ሁሉም ከእኛ ወገን እንዳልነበሩ
ይታወቅ ዘንድ ከእኛ ተለዩ::
20እናንተ ግን ከእርሱ ከቅዱሱ፣ ቅባት
አላችሁና፤ ሁላችሁም እውነትን[ሡ] ታውቃላ
ችሁ:: 21እኔ የምጽፍላችሁ እውነትን ስለ
ማታውቁ አይደለም፤ ነገር ግን እውነትን
ስለምታውቁትና ከእውነት ምንም ውሸት
ስለማይወጣ ነው:: 22ክርስቶስ አይደለም
ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ሐሰተኛ
ማነው? ይህ አብንና ወልድን የሚክደው
የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው:: 23ወልድን የሚ
ክድ ሁሉ አብ የለውም፤ ወልድን የሚያ
ምን ሁሉ አብም አለው::
24ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ
ውስጥ ይኑር፤ ከመጀመሪያ የሰማችሁት
በእናንተ ውስጥ ቢኖር፣ እናንተም በወልድና
በአብ ትኖራላችሁ:: 25ይህ እርሱ የሰጠን
ተስፋ የዘላለም ሕይወት ነው::
26ስለሚያስቷችሁ ሰዎች ይህን ጽፌላች
ኋለሁ:: 27እናንተ ግን ከእርሱ የተቀበላች
ሁት ቅባት በውስጣችሁ ይኖራልና፤ ማንም
እንዲያስተምራችሁ አያስፈልግም፤ ነገር
ግን እውነት እንጂ ሐሰት ያልሆነው የእ
ርሱ ቅባት ስለ ሁሉም ነገር እንደሚያስተ
ምራችሁ፣ ያም እውነት እንጂ ሐሰት እን
ዳልሆነ፣ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእ
ርሱ ኑሩ::

### የእግዚአብሔር ልጆች

28እንግዲህ ልጆች ሆይ፤ እርሱ ሲገለጥ
ድፍረት እንዲኖረን፣ በሚመጣበትም ጊዜ
በፊቱ እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ::
29እርሱ ጻድቅ መሆኑን ካወቃችሁ፣ ጽድ
ቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደ ተወ
ለደ ታውቃላችሁ::

3 የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ
አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር
ምንኛ ታላቅ ነው! እኛም እንዲሁ ልጆቹ
ነን:: ዓለም እኛን የማያውቀንም እርሱን
ስላላወቀው ነው:: 2ወዳጆች ሆይ፤ እኛ
አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደ ፊት
ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም::
እርሱ በሚገለጥበት[ረ] ጊዜ እናየዋለንና፣
እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን:: 3በእ
ርሱ ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ
ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል::
4ኀጢአት የሚያደርግ ሁሉ ዐመፅን ያደ
ርጋል፤ ኀጢአትም ዐመፅ ነው:: 5እርሱ
ኀጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታው
ቃላችሁ፤ በእርሱም ኀጢአት የለም:: 6በእ
ርሱም የሚኖር ኀጢአትን አያደርግም፤
ኀጢአት የሚያደርግ ግን እርሱን አላየ
ውም ወይም አላወቀውም:: 7ልጆች ሆይ፤
ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ እርሱ
ጻድቅ እንደ ሆነ፣ ጽድቅን የሚያደርግ
ጻድቅ ነው:: 8ኀጢአትን የሚያደርግ ከዲያ
ብሎስ ነው:: ምክንያቱም ዲያብሎስ ከመ
ጀመሪያ አንሥቶ ኀጢአትን የሚያደርግ
ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠውም የዲ
ያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ ነው:: 9ከእግ
ዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአትን አያደር
ግም፤ የእርሱ ዘር በውስጡ ይኖራልና፤
ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደም ኀጢአትን ሊያ
ደርግ አይችልም:: 10የእግዚአብሔር ልጆችና
የዲያብሎስ ልጆች ተለይተው የሚታወ
ቁት በዚህ ነው:- ጽድቅን የማያደርግ፣
ወንድሙንም የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር
አይደለም::

### እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ

11ከመጀመሪያ የሰማችኋት፣ እርስ በር
ሳችን ልንዋደድ ይገባናል የምትለዋ መል
እክት ይህች ናትና፤ 12የክፉው ወገን ሆኖ
ወንድሙን እንደ ገደለው እንደ ቃየን አት
ሁኑ፤ ለምን ገደለው? ምክንያቱም የእርሱ
ሥራ ክፉ፣ የወንድሙ ግን ጽድቅ ስለ
ነበረ ነው:: 13ወንድሞች ሆይ፤ ዓለም ቢጠ
ላችሁ አትደነቁ:: 14ወንድሞቻችንን ስለም
ንወድ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገ
ርን እናውቃለን፤ ፍቅር የሌለው ሁሉ
በሞት ይኖራል:: 15ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ
ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይ
ወት እንደሌለው ታውቃላችሁ::
16ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ
አሳልፎ ስለ ሰጠ፣ ፍቅር ምን እንደ ሆነ
በዚህ እናውቃለን፤ እኛም ሕይወታችንን

2፥16 ዘፍ3፥6፤ ምሳ 27፥20፤ ሮሜ13፥14፤ኤፌ2፥3
2፥17 ማቴ12፥50፤ ዕብ12፥27
2፥18 ቍ22፤ ሮሜ13፥11፤ 1ዮሐ4፥1:3፤2ዮሐ7
2፥19 ሐሥ20፥30፤ 1ቆሮ11፥19
2፥20 ቍ27፤ኤር 31፥34፤ማቴ13፥11፤ ማር1፥24፤ዮሐ14፥26 ፤2ቆሮ1፥21
2፥21 2ጴጥ1፥12፤ ይሁ5
2፥22 1ዮሐ4፥3፤ 2ዮሐ7
2፥23 ዮሐ8፥19፤ 14፥7፤ 1ዮሐ4፥15፤ 5፥1፤2ዮሐ9
2፥24 ቍ7፤ ዮሐ 14፥23፤15፥4፤ ዮሐ 1፥3፤2ዮሐ9
2፥25 ማቴ25፥46
2፥26 1ዮሐ3፥7
2፥27 ቍ20፤ዮሐ 15፥4፤ 1ቆሮ2፥12
2፥28 ቍ1፤ ኤፌ3፥12፤ቈላ3፥4፤ 1ተሰ2፥19፤1ዮሐ3፥2
2፥29 ዮሐ1፥13፤ 1ዮሐ3፥7
3፥1 ቍ2:10፤ ዮሐ 1፥12፤3፥16፤ 15፥21፤ 16፥3
3፥2 ቍ1:10፤ መዝ17፥15፤ ዮሐ1፥12፤17፥24፤ ሮሜ8፥29፤ 1ቆሮ10፥14፤ 2ቆሮ3፥18፤ቈላ3፥4፤ 2ጴጥ1፥4፤1ዮሐ2፥28
3፥3 መዝ18፥26፤ 2ቆሮ7፥1፤ 2ጴጥ3፥13:14
3፥4 1ዮሐ5፥17
3፥5 ቍ8፤ዮሐ3፥17 ፤2ቆሮ5፥21
3፥6 ቍ9፤1ዮሐ2፥4 ፤5፥18፤3ዮሐ11
3፥7 1ዮሐ21:6:29
3፥8 ቍ10፤ማቴ4፥3 ፤ዮሐ8፥44፤ዕብ2፥14
3፥9 ቍ6፤መዝ119፥3 ፤ዮሐ1፥13፤1ጴጥ1፥2 3፤1ዮሐ5፥18
3፥10 ቍ1:2:8፤ዮሐ 1፥12፤1ዮሐ2፥9፤4፥8
3፥11 ዮሐ13፥24: 35፤15፥12፤1ዮሐ1፥5 ፤2፥7፤4፥7:11:21፤ 2ዮሐ5
3፥12 ዘፍ4፥8፤መዝ 38፥20፤ምሳ29፥10፤ ማቴ5፥37
3፥13 ዮሐ15፥18:1 9፤17፥14
3፥14 ዮሐ5፥24፤ 1ዮሐ2፥9
3፥15 ማቴ5፥21:22 ፤ዮሐ8፥44፤ገላ5፥20:21 ፤1ዮሐ2፥9፤ራእ21፥8

3፥16 ዮሐ10፥11፤15፥13፤ፊል2፥17፤1ተሰ2፥8

ሠ5 ወይም *ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር* ማለት ነው::
ሡ20 አንዳንድ ቅጆች፣ *እናንተ ሁሉንም ነገር ታውቃላችሁ* ይላሉ::
ረ2 ወይም *በሚታወቅበት ጊዜ*

ስለ ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባ
ናል። [17]ማንም ሀብት እያለው፣ ወንድሙ
ሲቸገር አይቶ ባይራራለት፣ የእግዚአብሔር
ፍቅር እንዴት በእርሱ ይኖራል? [18]ልጆች
ሆይ፤ በተግባርና በእውነት እንጂ በቃልና
በአንደበት ብቻ አንዋደድ። [19]እኛ የእው
ነት ወገን መሆናችንን በዚህ እናውቃለን፤
ልባችንንም በፊቱ እናሳርፋለን፣ [20]ይህም
ልባችን በእኛ ላይ በሚፈርድብን ነገር ሁሉ
ነው። እግዚአብሔር ከልባችን ይልቅ ታላቅ
ነውና ሁሉን ነገር ያውቃል።

[21]ወዳጆች ሆይ፤ ልባችን የማይፈርድ
ብን ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ድፍረት አለን፤
[22]ትእዛዛቱንም ስለምንጠብቅና በፊቱም ደስ
የሚያሰኘውን ስለምናደርግ የምንለምነ
ውን ሁሉ ከእርሱ እንቀበላለን። [23]ትእዛዙም
በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እንድናምንና
እርሱ እንዳዘዘንም እርስ በርሳችን እንድንዋ
ደድ ነው። [24]ትእዛዞቹንም የሚጠብቁ ሁሉ
በእርሱ ይኖራሉ፤ እርሱም በእነርሱ ይኖ
ራል። በእኛ መኖሩን በዚህ ይኸውም
እርሱ በሰጠን መንፈስ እናውቃለን።

### መናፍስትን መርምሩ

4 ወዳጆች ሆይ፤ መንፈስን ሁሉ አት
መኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር
መሆናቸውን መርምሩ፤ ምክንያቱም ብዙ
ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋ
ልና። [2]የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታው
ቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ
መጣ የሚቀበል መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር
ነው፤ [3]ኢየሱስን የማይቀበል መንፈስ ግን
ከእግዚአብሔር አይደለም፤ እንደሚመጣ የሰማ
ችሁት የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ይህ
ነው፤ አሁንም እንኳ በዓለም አለ።

[4]ልጆች ሆይ፤ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ፤
እነርሱንም አሸንፋችኋቸዋል፤ ምክንያ
ቱም በእናንተ ውስጥ ያለው በዓለም ካለው
ይበልጣል። [5]እነርሱ ከዓለም ናቸው፤ ስለ
ዚህ የሚናገሩት እንደ ዓለም ነው፤ ዓለ
ምም ይሰማቸዋል። [6]እኛ ከእግዚአብሔር ነን፤
እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአ
ብሔር ያልሆነ ግን አይሰማንም፤ በዚህም
የእውነትን መንፈስና የሐሰትን መንፈስ
እናውቃለን።

### የእግዚአብሔር ፍቅርና የሰው ፍቅር

[7]ወዳጆች ሆይ፤ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለ
ሆነ እርስ በርሳችን እንዋደድ፤ የሚወድ
ሁሉ ከእግዚአብሔር የተወለደ ነው፤ እግዚአ
ብሔርንም ያውቃል። [8]የማይወድ ግን እግዚ
አብሔርን አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።
[9]እግዚአብሔር ፍቅሩን በመካከላችን የገለጠው

3፥17 ዘዳ15፥7፡8፤ ያዕ2፥15፡16፤ 1ዮሐ4፥20
3፥18 ሕዝ33፥31፤ ሮሜ12፥9፤1ዮሐ2፥1
3፥21 1ቆሮ10፥14፤ ኤፌ3፥12፤1ዮሐ5፥14
3፥22 ማቴ7፥7፤ ዮሐ8፥29፤14፥15፤ ዕብ13፥21
3፥23 ሉቃ24፥47፤ ዮሐ1፥12፤3፥18፤ 6፥29፤13፥34፤20፥3 1ቆሮ6፥11፤1ዮሐ5፥13
3፥24 1ተሰ4፥8፤ 1ዮሐ 2፥3፡6፤ 14፥13፡15
4፥1 ኤር29፥8፤ ማቴ7፥15፤1ቆሮ10፥14 ፤12፥10፤2ተሰ2፥2፤ 1ዮሐ2፥18
4፥2 ዮሐ1፥14፤1ቆሮ 12፥3፤1ዮሐ2፥23
4፥3 1ዮሐ2፥18፡ 22፤2ዮሐ7
4፥4 2ነገ6፥16፤ ዮሐ12፥31፤16፥33፤ ሮሜ8፥31፤1ዮሐ2፥1
4፥5 ዮሐ15፥19፤ 17፥14፡16
4፥6 ማር13፥5፤ ዮሐ8፥47፤14፥17
4፥7 ዮሐ1፥13፤ 1ዮሐ2፥4፤3፥11
4፥8 ቍ7፡16
4፥9 ዮሐ1፥18፤ 3፥16፡17፤1ዮሐ5፥11
4፥10 ሮሜ3፥25፤ 5፥8፡10
4፥11 ዮሐ3፥16፤ 15፥12፤1ቆሮ10፥14፤ 1ዮሐ3፥11
4፥12 ቍ17፤ ዮሐ1፥18፤1ዮሐ2፥5
4፥13 1ዮሐ2፥3፤ 3፥24
4፥14 ሉቃ2፥11፤ ዮሐ3፥17፤15፥27
4፥15 1ዮሐ2፥23፤ 3፥24፤5፥5
4፥16 ቍ8፡12፡1 3፤1ዮሐ3፥24
4፥17 ቍ12፤ ማቴ10፥15፤ ኤፌ3፥12፤1ዮሐ2፥5
4፥18 ሮሜ8፥15
4፥19 ቍ10
4፥20 ቍ12፤ ዮሐ1፥18፤1ዮሐ1፥6፤ 2፥4፡9፤3፥17
4፥21 ማቴ5፥43፤ 1ዮሐ2፥7፡9
5፥1 ዮሐ1፥13፤ 3፥15፤8፥42፤ 1ዮሐ2፥22፡23፤ 4፥2፡15
5፥2 1ዮሐ2፥3፤ 3፥14
5፥3 ማቴ11፥30፤ 23፥4፤ዮሐ14፥15
5፥4 ዮሐ1፥13፤ 16፥33

እንዲህ ነው፤ እኛ በእርሱ አማካይነት በሕ
ይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድያ
ልጁን ወደ ዓለም ላከ። [10]ፍቅር ይህ ነው፤
እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን
እርሱ እንደ ወደደንና ስለ ኀጢአታችን
ማስተስረያ[ሰ] ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ
ነው። [11]ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ
ከወደደን፣ እኛም እርስ በእርሳችን መዋ
ደድ ይገባናል። [12]እግዚአብሔርን ያየ ከቶ
ማንም የለም፤ እርስ በርሳችን ብንዋደድ
ግን እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል፤ ፍቅሩም
በእኛ ፍጹም ይሆናል።

[13]መንፈሱን ስለ ሰጠን፣ እኛ በእርሱ
እንደምንኖር እርሱም በእኛ እንደሚኖር
እናውቃለን። [14]አብ ልጁን የዓለም አዳኝ
ይሆን ዘንድ እንደላከው ዐይተናል፤ እንመ
ሰክራለንም። [15]ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ
እንደ ሆነ አምኖ በሚመሰክር ሁሉ፣ እግዚ
አብሔር በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም በእግዚአ
ብሔር ይኖራል። [16]ስለዚህም እግዚአብሔር ለእኛ
ያለውን ፍቅር እናውቃለን፤ በፍቅሩም እና
ምናለን።

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅር የሚ
ኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፤ እግዚአብሔርም
በእርሱ ይኖራል። [17]በዚህም ዓለም እርሱን
እንመስላለንና። በፍርድ ቀን ድፍረት ይኖ
ረን ዘንድ፣ ፍቅር በዚህ ዐይነት በመካከላ
ችን ፍጹም ሆኖአል፤ [18]በፍቅር ፍርሀት
የለም፤ ፍጹም ፍቅር ግን ፍርሀትን አው
ጥቶ ይጥላል፤ ፍርሀት ከቅጣት ጋር የተያ
ያዘ ነውና። የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም
አይደለም።

[19]እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እን
ወደዋለን። [20]ማንም፣“እግዚአብሔርን እወደዋ
ለሁ” እያለ ወንድሙን ቢጠላ፣ እርሱ ሐሰ
ተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ
ያላየውን እግዚአብሔርን መውደድ አይችል
ምና። [21]እርሱም “እግዚአብሔርን የሚወድ
ሁሉ ወንድሙን መውደድ ይገባዋል” የሚለ
ውን ይህን ትእዛዝ ሰጥቶናል።

### በእግዚአብሔር ልጅ ማመን

5 ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ
የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶ
አል፤ አባትንም የሚወድ ሁሉ ልጁንም
እንደዚሁ ይወዳል። [2]እግዚአብሔርን ስንወድና
ትእዛዛቱን ስንፈጽም የእግዚአብሔርን ልጆች
እንደምንወድ በዚህ እናውቃለን፤

[3]እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዛቱን መፈ
ጸም ነውና። ትእዛዛቱም ከባድ አይደ
ሉም፤ [4]ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተወለደ

[ሰ]10 ወይም ኀጢአታችንን አስወግዶ፣ ቍጣውን ያርቅልን ዘንድ

ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል፡፡ ዓለምን የሚያሸ
ንፈውም እምነታችን ነው፡፡ [5]ኢየሱስ የእግዚ
አብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን በስተ
ቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው?
[6]በውሃና በደም የመጣው ይህ፣ ኢየ
ሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ በውሃና በደም
እንጂ በውሃ ብቻ አልመጣም፡፡ የሚመሰክ
ረውም መንፈስ ነው፤ መንፈስ እውነት
ነውና፡፡ [7]ስለዚህ ሦስት ምስክሮች አሉት፡፡
[8]እነርሱም[ሸ] መንፈሱ፣ ውሃውና ደሙ ናቸው፤
ሦስቱም ይስማማሉ፡፡ [9]የሰውን ምስክርነት
ከተቀበልን፣ የእግዚአብሔር ምስክርነት ከዚያም
ይልቃል፤ ይህ ስለ ልጁ የሰጠው የእግዚአብሔር
ምስክርነት ነውና፡፡ [10]በእግዚአብሔር ልጅ የሚ
ያምን ሁሉ በልቡ ምስክር አለው፤ ማንም
እግዚአብሔርን የማያምን ሁሉ እግዚአብሔር ስለ
ልጁ የሰጠውን ምስክርነት ስላላመነ ሐሰ
ተኛ አድርጎታል፡፡ [11]ምስክርነቱም ይህ ነው፤
እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት ሰጠን፤ ይህም
ሕይወት ያለው በልጁ ነው፡፡ [12]ልጁ ያለው
ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌ
ለው ሕይወት የለውም፡፡

## ማጠቃለያ ሐሳብ

[13]በእግዚአብሔር ልጅ ስም የምታምኑ እና
ንተ፣ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ
ዘንድ ይህን እጽፍላችኋለሁ፤ [14]በእግዚአብሔር
ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤

5፥5 ቆላ1፤ 1ዮሐ2፥23
5፥6 ዮሐ14፥17፤ 19፥34
5፥7 ማቴ18፥16
5፥9 ማቴ3፥16፡17፤ ዮሐ5፥32፡34፡37፤ 8፥17፡18
5፥10 ዮሐ3፥33፤ ሮሜ8፥16፤ ገላ3፥6፤1ዮሐ1፥10
5፥11 ማቴ25፥46፤ ዮሐ1፥4
5፥12 ዮሐ3፥15፡ 16፡36
5፥13 ቆላ11፤ ማቴ25፥46፤ 1ዮሐ3፥23
5፥14 ማቴ7፥7፤ ኤፌ3፥12፤ 1ዮሐ3፥21
5፥15ቆላ18፡19፡20፤ 1ነገ3፥12
5፥16 ዘፀ23፥21፤ ኤር7፥16፤ 14፥11፤ዕብ6፥4-6፤ 10፥26፤ያዕ5፥15
5፥17 ቆላ16፤ ዮሐ2፥1፤3፥4
5፥18 ማቴ5፥37፤ ዮሐ1፥13፤14፥30
5፥19 ዮሐ12፥31፤ 14፥30፤17፥15፤ 1ዮሐ4፥6
5፥20 ቆላ5፡11፤ ማቴ25፥46፤ ሉቃ24፥45፤ዮሐ17፥3
5፥21 1ቆሮ10፥14፤ 1ተሰ1፥9፤1ዮሐ2፥1

ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን
እርሱ ይሰማናል፤ [15]የምንለምነውን ሁሉ
እንደሚሰማን ካወቅን፣ የለመነውንም ነገር
እንደ ተቀበልን እናውቃለን፡፡
[16]ማንም ሰው ወንድሙ ለሞት የማያ
በቃ ኀጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይጸልይ፤
እግዚአብሔርም ለሞት የማያበቃ ኀጢአት ላደ
ረጉት ሕይወትን ይሰጣል፡፡ ለሞት የሚያ
በቃም ኀጢአት አለ፤ ስለዚህኛው ግን ይጸ
ልይ አልልም፡፡ [17]ዐመፅ ሁሉ ኀጢአት ነው፤
ለሞት የማያበቃም ኀጢአት አለ፡፡ [18]ከእግዚ
አብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአት እንደማያደ
ርግ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚጠ
ብቀው፣ ክፉውም እንደማይነካው እናውቃ
ለን፡፡ [19]እኛ ከእግዚአብሔር እንደሆንን፣ መላው
ዓለምም በክፉው ሥር እንደ ሆነ እናው
ቃለን፡፡
[20]የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣ፣ እውነ
ተኛ የሆነውን እርሱን እንድናውቅ ማስተ
ዋልን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እኛም እው
ነተኛ በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ
አለን፡፡ እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም
ሕይወት ነው፡፡
[21]ልጆች ሆይ፤ ራሳችሁን ከጣዖቶች ጠብቁ፡፡

[ሸ]7፡8 ጥንታዊ ባለሆነ በቍልጌት ቅጅ ላይ *በሰማይ የሚመሰክሩት ሦስቱ ናቸው፤ እነርሱም አባት፤ ቃልና መንፈስ ቅዱስ ናቸው* ይላል፡፡
8. በምድር የሚመሰክሩት ሦስቱ ናቸው (ሆኖም ይህ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በነበሩት የግሪክ ቅጆች ውስጥ አይገኝም፡፡